የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፯
አዲስ አበባ ሰኔ ፱ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No. 47
ADDIS ABABA, 16th June 2017

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፳፫/፪ሺ፱ ዓ.ም

ለአራኛው ልማታዊ የሴፍቲኔት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል የተጨማሪ ብድር ከአለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የሁለተኛ የተጨማሪ ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ................................................... ገፅ ፱ሺ፮፻፷፭

CONTENT

Proclamation No.1023/2017

International Development Association Loan Agreement for Financing the Second Additional Financing Agreement for additional Financing the Second Additional Financing for Productive Safety Net Project IV Ratification. proclamation...........................................................page 9665

## አዋጅ ቁ□ር ፩ሺ፳፫/፪ሺ፱

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በአለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለአራኛው ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፸፱ ሚሊዮን ፯፻ሺ ኤስ.ዲ. አር (ሰባ ዘጠኝ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) ሁለተኛ ተጨማሪ ብድር የሚያስገኘው ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በአለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ግንቦት ፩ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

## PROCLAMATION No.1023 /2017

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCAITION

**WHERE AS**, a Loan Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association Stipulating that the International Development Association shall provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia an additional loan amount of SDR 79,700,000(seventy nine million seven hundred thousand SDR) for financing the Second Additional Financing for Productive Safety Net Project IV was signed in Addis Ababa on the 9th day of May 2017;

**WHERE AS,** the House of the Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Loan Agreement at its

ግንቦት ፳፬ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀፅ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

**፩.<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለአራኛው ልማታዊ የሴፍቲኔት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል የተጨማሪ ብድር ከአለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የሁለተኛ የተጨማሪ ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፳፫/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪.<u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በአለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ግንቦት ፩ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው ሁለተኛ የተጨማሪ ብድር ስምምነት ቁጥር 6041E.T በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫.<u>የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ስልጣን</u>**

የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፸፱ ሚሊዮን ፯፻ሺ ኤስ ዲ አር (ሰባ ዘጠኝ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺ ኤስ ዲ አር) ተጨማሪ ብድር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፱ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

session held on the 16th day of May 2017;



**NOW THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. **<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for Financing the Second Additional Financing for Productive Safety Net Project IV Ratification Proclamation No.1023/2017"

2. **<u>Ratification of the Agreement</u>**

The Financing Agreement Number 6041-ET signed in Addis Ababa on the 9th day of May, 2017 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

3. **<u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of SDR 79,700,000 (seventy nine seven hundred thousand SDR) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. **<u>Effective Date</u>**

Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 16th day of June 2017**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**